# ሌ/ኮለኔል ጌትየ አለሜ ላይ የደረሰው ግፍ !!!

# መቋጫ ያጣው ግፍና መከራ በአማራ!

ሰሞኑን ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ቴሌቪዥን ጋዜጠኞች በእስር ቤት የደረሰበትን ግፍ የገለፀው ጌትየ አለሜ ህክምና እንደተቋረጠበት ገልጧል።

የቀኝ እግሩ አራት ቦታ ላይ በጥይት የተበሳሳው የወሎ መቄት ወረዳ ተወላጁ ጌትየ አለሜ ሰኔ 20 ቀን 2010 ዓ•ም ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በእስር ቤት ቆይታው በአካል፣በሞራልና በስነ ልቦና የደረሰበትን ጉዳት ለጋዜጠኞች አካፍሎ መተላለፉን ተከትሎ በ2006 ዓ•ም የህወሐት የእስር ቤት አመራሮች በሽጉጥ ጥይት የተመታው እግሩ ወደ ካንሰርነት እንዳይቀየርበት የታዘዘለትን መርፌ ለ2 ቀናት ያህል እንዳቋረጡበት እና ህመሙ እየባሰበት መሆኑን ተናግሯል።

ከ1978 ዓ•ም ጀምሮ በኢህዴን ታጋይነት የተጣለበትን ሀላፊነት ሲወጣ የቆየ መሆኑን የገለፀው ጌትየ ከሚደርስበት ከባድ የሰብአዊ መብት ጥሰት ለመላቀቅ በ2006 ዓ•ም ከቂሊንጦ የማምለጥ ሙከራ ማድረጉን ተከትሎ ከ8 ቀናት በኃላ ይያዛል።
የያዙት የፌደራል ፖሊስና የደህንነት አካላት በአካሉ ላይ ምንም ጉዳት ሳያደርሱ ለማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ አሳልፈው እንደሰጡት ያስታውሳል።

ከተያዘ በኃላ ግን ከዳንግላ የመጣውን የአማራ ተወላጅ ሾፌር አዲስ አበባ መሀል ከተማ ላይ በማስወረድ የራሳቸውን አንድ የትግራይ ተወላጅ ሾፌር አስገብተው ወደ ቂሊንጦ እንዲነዳው ያደርጋሉ።የሆነ ተንኮል ማሰባቸው ግልፅ እየሆነልኝ መጣ ይላል።
ከማዕከላዊ የሰዓታት ቆይታ በኃላ ተላልፎ ለቂሊንጦ እስር ቤት መሰጠቱን ተከትሎ ሻቢያ የተባለ የህወሐት ወታደር በሽጉጡ አፈሙዝ አይኔ ላይ መታኝ፣ሙሉ ፊቴ ደም በደም ሆነ፣ይህ መግቢያ መሆኑ ነው ሲል የደረሰበትን በደል ይዘረዝራል።
በውስጡ ሻቢያ፣አምባየ፣ማሞ፣ገ/ማርያም እና ስሙን የማያውቀው አንድ የትግሬ ሹፌር ብቻ አሉ። በትግርኛ ያወራሉ።ስልክ ይደዋወላሉ።በጠራራ ፀሀይ እጅ እና እግሩን ካሰሩ በኃላ ሻዕቢያ፣አምባየ እና ማሞ ለሶስት እንደሚታረድ በሬ ጥለው በሶስት የሽጉጥ ጥይት እግሩን እንደሰበሩት ተናግሯል። የአንደኛው ሽጉጥ ጥይት መርዛማ እና አደገኛ ነበር ይላል።

ሾፌሩ ክላሽ ደቅኖ መቆሙን አስተውሳለሁ ሲል ይናገራል ፣በመቀጠልም ለመቀጣጫ ተብሎ በቂሊንጦ ዞን ሁለት ደሙን እያዘሩ ይወስዱታል።ዞን ሁለት ያሉ እስረኞች ይበሳጫሉ፣በጥይት ያቆሰላቹሀትን ሰው ወደ ህክምና መውሰድ ሲገባ ወደ እስር ቤት ለምን ታመጡታላቹህ በሚል የተናገሩ እነ አበበ ካሴ፣ዶ/ር ፍቅሩ ማሩና አኬሎ አኳይ እንደተቀጡ ገልጧል።
ከዞን ሁለት አውጥተው ወደ ዞን አንድ እና ሶስት ሲወስዱት እስረኛው የግቢውን በር በመዝጋት ተቃውሞውን ይገልፃል፣ወስደው ከክሊኒኩ አጠገብ እንደጣሉት እና ደሙ እየፈሰሰ ብርድ ሲፈራረቅበት አደርኩ ይለናል።

በማግስቱ ቁርስ የሚያመጡ እስረኞች/ኅለኞች/ ሲወጡ ወድቆ ያዩታል፣ምግብ መውሰዳቸውን ትተው ወደ ግቢ ገብተው ለእስረኞች ይናገራሉ።እስረኛው ይጮህል፣ ጌትየን አንስተው ወደ ቃሊቲ ይወስዳሉ፣ ልብ በሉ ደሜ እየፈሰሰ እንኳ ቶሎ ወደ ህክምና ማስገባቱን ትተው ፎቶ ለማንሳት ይሯሯጡ ነበር ብሏል።አሳዛኝ ነው እንድሞት ነበር ፍላጎታቸው በማለት በደሉን አጋልጧል።
ወደ ቃሊቲ ሆስፒታል ዘግይተውም ቢሆን አስገቡኝ፣እያከሙኝ ሳለ እግሬን በካቴና ከክብደት መስሪያ እንጨት ጋር አቆራኙ፣እጆቸን በካቴና አሰሩ፣ያቆሰሉኝና አንዳንድ ማላውቃቸው ሰዎች ከሌሊቱ ሰባትና

ስምንት ስዓት ሆስፒታል እየመጡ ከግድግዳው ጋር ያጋጩኛል፣ይደበድቡኛል።

በሶስተኛ ቀኔ ሀኪሙ ሳይፈቅድ ከተኛሁበት ህክምናውን አቋርጠው ወሰዱኝ።ለሶስት ወር ያህል ህክምናው ተቋርጦ ሰውነቴ ሸተተ፣ሽንት ቤት የሚወስደኝ ሰው ተቸገረ።
ሀኪሞቹ ወደ ጋንግሪን እንደሚቀየርብኝ ከነገሯቸው በኃላ በስንት ትግል ወደ ፖሊስ ሆስፒታል እንድሄድ ተፈቀደ•••
እያለ ነበር ቂም ያረገዘው አማራ ጠላቴ ነው ብሎ የተነሳው ስርዓት ባለአደራዎች በመተባበር ያለማንም ሀይ ባይ ያደረሱበትን ጥቃት ከአራት ዓመት በኃላ በተፈቀደለት የብረት ክራንች ከቃሊቲ ዞን አንድ መጥቶ ያነጋገረን!

በእውነት አንጀት ይበላል! ያስለቅሳል!በጥይት የተመታው የቀኝ እግሩ አጥሯል፣አርቲፊሻል ጫማ እንደታዘዘለት ነግሮናል።ቀይ መስቀል ያዘዘለትን የአሉምኒየም ክራንች በብረት የቀየሩበት መሆኑን የቀይ መስቀል ሀኪሞች እንደነገሩት እያዘነ አጫውቶናል።ይህን ግልፅ ወንጀል የፈፀሙት ሰዎች በህግ አልተጠየቁም፣አሁንም በስራ ላይ ሆነው በቂሊንጦና በቃሊቲ እንደሚገኙ ይናገራል፣አንዳንዶችም እያንገራግሩት እንደሚኖሩ ተናግሯል።

ጌታየ አለሜ የሌተናል ኮሎኔልነት ማዕረጉ በቆራጣ ደብዳቤ ተነስቶበታል።



